# የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር

ዘመን የሚባለዉ የእድሜ ቀጠሮ ከስያሜዉ አንጻር ለሦስት ወገን ይከፈላል:: ይኸዉም ያለፈዉ ያሁን እና የሚመጣዉ ዘመን ነዉ:: ዘመን በአምስት መስፈሪያ ወይም መቁጠሪያ ይከፈላል:: ይህም፡- ዓመት ወር ሳምንት ዕለት ሰዓት ነዉ:: እንደ ኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር አንድ ዕለት የሚጀምረዉ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ነዉ::

ዘመን ለሰዉ ልጅ ከዘመናት ባለቤት እግዚአብሔር የተሰጠ ነዉ:: ይህንም ቅዱስ መጽሐፍ « እግዚአብሔር ለሰዎች ዓመታትንና ዘመናትን በቁጥር ሰጣቸዉ» (ሲራክ 17:3)

- ከአዳም እስከ ኖህ 2200 ዓመት
- ከኖህ እስከ ሙሴ 1656
- ከሙሴ እስከ ልደተ ክርስቶስ 1644
- ይህም ሲደመር 5500 ዓመት ይሆናል::

ከልደተ ክርስቶስ አስቀድሞ የነበረዉ ዘመን ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ ዘመነ ብሉይ ይባላል:: ይኸዉም ዘመነ መሲህ ነዉ:: ክርስቶስ ይወርዳል ይወለዳል እዬተባለ ትንቢት የተነገረበት:: ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ ያለዉ ዘመን ዓመተ ምሕረት ይባላል:: መላዉ ግን ዓመተ ዓለም መዋዕለ ዓለም ይባላል:: ኢትዮጵያ ዘመነ ብሉይን 5500 ዘመን ማለቷ በበጥሊሞስ ዘመን ሰብዐ ሊቃናት ከጥንታዊ እብራይስጥ ወደ ዮናኒ የመለሱትን (የተረጎሙትን) መጽሐፈ ኦሪትን (ኦሪተ ግእዝን) ተከትላ ነዉ:: ኢትዮጵያ ይዛዉ የምትገኘዉ ኦሪተ ግእዝም ዘመነ አበዉና ዘመነ መሳፍንት ዘመነ ነገሥትና ዘመነ ካህናትን ሳያዛባና ሳያንድል በጥንቃቄ ይዞ እንደሚገኝ ይታመንበታል:: ኢትዮጵያዉያን ከጥንት ጀምሮ በዓመት ዉስጥ ያሉትን አራቱን ክፍላተ ዓመት በ91 በ91 ቀናት መድቦ ስያሜያቸዉንና ትርጓሜያቸዉን እንደዚሁም መጋቢዎቻቸዉን ከዋክብት ለይቶ ማወቅና ማስረዳት የኢትዮጵያዉያን የራሳቸዉ የሆነ የዘመናት አመዳደብና አቆጣጠር ጥበብ ነዉ:: (ሄኖክ 28 15:24) የኢትዮጵያ ክፍላተ ዘመናት አመዳደብ የኢትዮጵያን ተፈጥሮአዊ የአዬር ጠባይ በሚያዉቁ ኢትዮጵያዉያን የሃሳበ ዘመን ሊቃዉንት የተመደበ ወይም የተቀመረ እንጂ ከሌላ የዉጭ ሰዉ የተወረሰ ወይም የተቀዳ አይደለም:: እነዚህ አራት ክፍላተ ዘመናትም መፀዉና ሐጋይ ፀደይና ክረምት ይባላሉ::

እንደ ኢትዮጵያዉያን አቆጣጠር ከመስከረም 1 ቀን ጀምሮ ያለንበት ዓመት ፡-

- በዓመተ ዓለም 7500 ዓመት ነዉ::
- በዓመተ ምሕረት 2000 ነዉ:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከልደተ ክርስቶስ በፊት የነበረዉን 5500 ዘመንና ከልደተ ክርስቶስ በኋላ የሚቆጠረዉን ዘመን በአንድነት እየደመረች በንኡስ

በማዕከላዊና በዐቢይ ቀመር እዬቀመረች ተንቀሳቃሽ በዓላትንና አጽዋማትን ለማዉጣት ትገለገልበታለች፡፡ ሌሎች አኃት አብያተ ክርስቲያናትም ይጠቀሙበታል፡፡

ከላይ በአጭሩ እንደተመለከተዉ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ይህን ሲመስል የምዕራባዉያን ዘመን አቆጣጠር በሰባት ወይም በስምንት ዓመት ከኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር በምን ምክኒያት ተለየ? የሚለዉን ተደጋጋሚ ጥያቄ በአጭሩ መልሰን ጽሁፋችንን እናጠቃል፡፡

- የምዕራባዉያን ዘመን አቆጣጠር ማዕከሉ ልደተ ክርስቶስ ነዉ፡፡ ይህም ማለት ከክርስቶስ ልደት በፊትና ከክርስቶስ ልደት በኃላ እዬተባለ የሚቆጠር ነዉ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንዳለዉ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከፍጥረተ አዳም ጀምሮ የሚቆጠር መነሻ የለዉም፡፡
- ያም ሆኖ ግን እስከ 532 ዓመተ ምሕረት ድረስ የሰባት ወይም የስምንት ዓመት ልዩነት ሳይኖር በምዕራቡም ሆነ በምሥራቁ ዓለም አኩል የሆነ የዘመን አቆጣጠር እንደነበረ ታዉቋል፡፡ በ532 ዓ.ም. የተነሳዉ ዲዮናስዮስ ኤክስጂዮስ የተባለዉ ሮማዊ ሊቅ መነኩሴ ከእርሱ በፊት ይታመንበት የነበረዉን የክርስቶስ ዓመተ ልደት በመለወጥ ወደኋላ ስምንት ዓመት ቀድሞ እንደተወለደ በመገመት ከነበረዉ የዘመን ቁጥር ስምንት ዓመት ጨመረ፡፡ ዲዮናሲዮስ አዲሱ አቆጣጠር ተግባራዊ እንዲሆን ያደረገዉም ከነበረበት ዘመን ወደ ኋላ ሂዶ በ276 ዓ.ም. ሲሆን 276 ይባል የነበረዉን 284 ሲል አዉጇል፡፡ ዲዮናስዮስ በ276 ላይ የጨመረዉን 8 ዓመት ከዬት እንዳመጣዉ ለመረዳት የሚደረገዉ ምርምር እንደቀጠለ ቢሆንም ዉጤቱ ምንም ይሁን ምን ግን ጭማሪዉ ለኢትዮጵያዉያን የዘመን አቆጣጠር ሊቃዉንት የሚዋጥ አይሆንም፡፡ ምክኒያቱም ጌታችን በሥጋ ያልተገለጠበትንና ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የነበረዉን የዓመተ ፍዳን ክፍል ዓመተ ምሕረት ብሎ ለመቀበል ስለሚያስቸግር ነዉ፡፡
- ክርስቶስ የተወለደዉ ኢትዮጵያ ከምትነሳበት ዓመት በፊት የ4 ወይም 7 ወይም 8 ዓመት ልዩነት /ቅድምና/ እንዳለ ይናገራሉ፡፡ይጽፋሉም፡፡ ኢትዮጵያ ግን በሰባት ወይም በስምንት ዓመት ልዩነት ወደ ኋላ ሁና የቀረች መስላ የምትታዬዉ ከላይ በአጭሩ እንደተገለጸዉ የግእዙንና የሰባ ሊቃናቱን ኦሪት መሠረት አድርጋ በራስዋ የመጽሐፍ ቅዱስ አቆጣጠር ስለምትቆጥር ነዉ፡፡
- ሌላዉ በኢትዮጵያና በምዕራባዉያን መካከል ያለዉ ልዩነት የቀናት ልዩነት ነዉ፡፡ ይኸዉም ከሰባት እስከ አሥር ቀን የሚሆን ልዩነት ነዉ ማቀትም በኢትዮጵያ መስከረም 1 ቀን ሲሆን በምዕራባዉያን መስከረም 11 ቀን ነዉ፡፡ ይህም ልዩነት የተጀመረዉ እንደ ኢትዮጵያዉያን በ 1575 ዓ.ም. እንደ አዉሮጳዉያን ደግሞ በ 1582 ዓ.ም በሮሙ ፓፓ በጎርጎርዮስ 13ኛ ነዉ፡፡ ከፓፓ ጎርጎሪዮስ በፊት የነበረዉ ካላንደር በ46 ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ሮምን ይገዛ የነበረዉ የቄሣር ዮልዮስ ካላንደር ነበር፡፡ እንደ ዮልዮሳዊ ካላንደር ዓመቱ 365 ቀናት ከስድስት ሰዓት ነበር፡፡ ፓፓ ጎርጎሪዮስ ግን ዓመቱ በሰከንድ በደቂቃ በሰዓትና በዕለት በጥንቃቄ ሲቀመር 365 ዕለታት ከ5 ሰዓት ከ48 ደቂቃዎችና ከ46 ሰከንዶች ይሆናል በማለት 11 ደቂቃዎችና 14

ሰከንዶች ሳይኖሩ እዬተኖረባቸዉ አልፈዋል ሲል ፓፓ ጎርጎሪዮስ አዲስ አቆጣጠር በመፍጠር ከሰባት እስከ አሥር ቀን ጨመረ:: ይህንንም ጭማሪ ጥቅምት 5 ቀን 1575 ዓ.ም. ኢትዮ. 1582 ዓ.ም. ጎርጎር 10 ቀን በመጨመር « ነገ ጥቅምት 15 ቀን 1582 ዓ.ም. ነዉ ብሎ » አወጀ:: እነዚህ 11 ደቂቃዎችና 14 ሰከንዶች ከጊዜ ብዛት ተጠራቅመዉ የዕለታትን ልዩነት እንደሚያመጡ በሁሉም ዘንድ ይገመታል::

የተወደዳችሁ ኢትዮጵያዉያን ሆይ! በዓለም ልዩ ከሚያደርገን ቅርሳችን መካከል አንዱ የዘመን አቆጣጠር ስልታችን በመሆኑ አባቶቻችን « ባለቤት ያቃለለዉን አሞሌ ባለእዳ አይሸከመዉም » እንዲሉ አጥብቀን መያዝና መጠበቅ እንዳለብን ለማስገንዘብ እወዳለሁ::የኢትዮጵያዉያንና የምዕራባዉያን ዘመን አቆጣጠር ልዩነት ከላይ በአጭር በአጭሩ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ ነዉ:: የአበዉ መጽሐፍትን አገላብጠን ታሪክ አመሳክረን መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ በቅርቡ በመጽሔት ያወጡትን ጥናታዊ ጽሁፍ አገናዝበን በአጭሩ ያጠናቀርልናችሁ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ይህ ነዉ::

የዘመናት ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር የምንጀምረዉን እሥራ ምዕት ዓመት የሰላምና የጤና የፍቅርና የደስታ የፍትሕና የነጻነት የስምምነትና የአንድነት የይቅርታና የበረከት ሺ ዓመት እንዲያደርግልን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን::

ተጻፈ በመ/ር መስፍን ብርሃኑ / B.Th., M.Phil.,Th.M./
ቶሮንቶ ካናዳ

# እንቁጣጣሽ

**እንቁጣጣሽ የሚለዉ የተጀመረዉ ንግሥተ ሳባ ወደ ሰሎሞን እጅ መንሻ እንቁ ይዛ ስትሔድ እሱም በበኩሉ ለጣጣሽ ብሎ ስጦታ ስላበረከተላት እንቁ ለጣጣሽ ወይም እንቁጣጣሽ ማለት ተጀመረ የሚሉ አሉ:: ወርኀ መስከረም የእንግጫ የአበባ ወቅት ስለሆነ ሕጻናት አበባ ይዘዉ የሚጫወቱበት በየጋራዉና ሸንተረሩ አደይ አበባ የሚፈነድቅበት ለምለም ሳርና ቅጠል የሚታይበት ምድር ከመታረስ ከመቆፈር የምታርፍበት ጨለማዉን ክረምት አልፈን ብርሃኑን በጋ የምንጀምርበትን ችዕሰ አዉደ ዓመት የምናከብርበት የዘመን መለወጫ ቀን ነዉ እንቁጣጣሽ::**

**የገብርኤሉ ነኝ**
**ከቶሮንቶ ካናዳ**